የወ/መ/ቁጥር 156219

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ አቶ ዘይኑ ኡመር በሽር - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ሐምሌ 27 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ግንቦት 17 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/09 ልዩ ቦታው የአብሥራ ሆቴል አካባቢ የግል ተበዳ በላይነሽ ማሞን አርድሻለሁ ብሎ በመናገሩ በፈፀመው የዛቻና ማስፈራራት ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሶትና ተነቦለት ከተረዳው በኋላ ክሱን ሳይቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብለው ክድው በመክራከራቸው ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የተሰሙት ምስክሮችም በክሱ ላይ በተመለከተው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ ተከሳሽ በመኪና እንጨት አስጭኖ ይዞ መጥቶ ሊያወርድ ሲል፤ እንጨቱ ሊራገፍበት የተባለው ቦታ ላይ የቧንቧ መስመር ስላለበት አይራገፍም በማለት ስናገረው ቆይ ጠብቂ አርድሻለሁ በማለት ተነግሯታል በማለት አስረድተዋል። በዚህም መሰረት ተከሳሽ በዚህ ድርጊታቸው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ስር እንዲከላከሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብለው አራት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ሲሆን የተሰሙበት ጭብጥም በወቅቱ የዛቻ ድርጊቱን አለመፈፀሜን፤ እንጨት በመኪና ጭኜ ለማውረድ ስሞክር የግል ተበዳይ አታራግፍም በማለት ከለከለችኝ ከዚያ በኋላ ሳይራገፍ ቀረ፤ በዚህ ጊዜም የተናገርኩት ነገር የለም በማለት አስመዝግበው አራቱ ምስክሮችም መኃላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ አስተባብለዋል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን ሁሉም የተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮች በወቅቱ ተከሳሽ እንጨት በመኪና አስጭኖ መጥቶ ለማራገፍ ሲሞክር የግል ተበዳይ እዚህ ቦታ አይራገፍም በማለት ስትከለክል ሹፌሩም ጭቅጭቅ ያለበት ቦታ አልቆምም በማለት ሄዷል በማለት አስረድተዋል። በዚህ ጊዜ ተከሳሽ የግል ተበዳይ ላይ የዛቻ የወንጀል ድርጊት ይፈፅም ወይም አይፈፅም በግልፅ ለማስረዳት ምስክሮቹ አልቻሉም። እንዲያውም አንደኛው ምስክር በወቅቱ ሱቅ ውስጥ ሆኖ ዕቃ እየሸጠ ስለነበር፤ ሁለተኛዋ ምስክር ደግሞ እዚሁ ሱቅ በር ላይ ሆና ዕቃ እየገዛች ስለመሆኑ የገለፁ

ስለሆነ በዚህ ሁኔታ ተከሳሽ የተናገሩትን ለመስማት እንደማይችሉ ፍ/ቤቱ ግንዛቤ ወስዷል። ሌሎቹ ምስክሮቹም እያንዳንዱን ተከሳሽና የግል ተበዳይ የተነጋገሩትን አልሰማንም ያሉ በመሆኑ ተከሳሽ ድርጊቱን አለመፈፀማቸውን ለማስረዳት አልቻሉም። በመሆኑም ተከሳሽ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበውን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል ያልቻሉ ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ የለንም፤ ነገር ግን ፍ/ቤቱ የወንጀል ደረጃውን ሲወስን ዝቅተኛ በማለት እንዲወስን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 55 ዓመት ነው፤ ትዳር አለኝ፤ ሥራዬ ንግድ ነው፤ በወር ብር 1500.00(አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ነው፤ አስር ልጆች አሉኝ በማለት አመለከቱ። ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ግራቀኙን በችሎት አነጋግሯቸው እንታረቅ ብለው በዚሁ መሰረት ታርቀው ቀርበው የግል ተበዳይ ማመልከቻ አያይዘው አቅርበዋል።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580/የዛቻ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም

መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው በቀንና ሰዎች በተሰበሰቡበት እንዲሁም ምንም አይነት ማጥቂያ መሳሪያ ሳይዝ በመሆኑ የወንጀል ደረጃው ቀላል ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 580 ለወንጀሉ የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከአስር ቀን እስከ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ቀላል እስራት የቅጣት እርዝመት ለአራት ተከፍሎ ስሌቱን በመስራት የተገኘው ውጤት ዝቅተኛ ደረጃ የሚለው የሚወድቀው ከአስር ቀን እስከ ሃምሳ ሁለት ቀን ባለው መካከል ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 13(7) መሰረት አርባ ቀን መነሻ ቅጣት ተብሎ ተወስኗል።

ይህ በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት በአባሪ አንድ እርከን 2 ላይ የሚታይ ሲሆን ፍቃደ ስልጣኑም/range/ ከአስር ቀን እስከ ሦስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት ሁለት ወር እስራት ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84 ወይም 85 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማክበጃ ያላቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ከላይ የተወሰነውን እርከን ከፍ አላደረገውም።

ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርብ ተጠይቆ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 ላይ በተገለፀት መሰረት አላቀረበም። በመሆኑም ከላይ የተመለከተውን እርከን ዝቅ አላደረገውም።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 2 ላይ በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን/range/ ከአስር ቀን እስከ ሦስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ባለመኖሩ በሁለት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ ከአሁን በፊት በሌላ የወንጀል ድርጊት ስለማይታወቁ፤ በንግድ ሥራቸው በርካታ የቤተሰብ አባላትን የሚያስተዳድሩ በመሆኑ፤ እንዲሁም በዛሬው ዕለት በችሎት ፊት ከግል ተበዳይ ጋር ታርቀውና በሰላም ለመኖር የተስማሙ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተከሳሽ አንድ ዕኩ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የወደፊት አመልና ፀባያቸውን ማየቱ በቂ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ስላመነ የእስራት ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 192 መሰረት በሁለት ዓመት ገደብ አግዶታል።

2 ኛ. ተከሳሽ የሁለት ዓመት ጊዜው እስኪጠናቀቅ ድረስ ቀድም ሲል ለዋስትና ያስያዙት የዋስትና ገንዘብ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 197(2) መሰረት ባለበት እንዲቆይ ታዟል።

3 ኛ. ተከሳሽ ለመንግስት የፅህፈት ወጪ ብር 50.00(ሃምሳ ብር) ለመንግስት

ይክፈሉ፤ ሲከፍሉም ይለቀቁ።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።